# የሼህ ሁሴን ጅብሪል ትንቢታዊ ግጥሞች*

©ጌቴ ገላዬ (ዶ/ር)

ሐምቡርግ ዩኒቨርሲቲ፥ ጀርመን
የአፍሪቃ እና የኢትዮጵያ ጥናቶች የትምህርት ክፍል
የአማርኛ ቋንቋ እና የአፍሪቃ ፎክሎር (ሥነቃል) መምህር
ነሐሴ 1996 ዓ.ም (August, 2004)

## መግቢያ

ከዚህ በታች የቀረቡት ግጥሞች የተገኙት በእጅ ተጽፎ ፎቶ ኮፒ ከተደረገ አንድ አነስተኛ ደብተር ላይ ነው:: ጽሑፉ መቼና በማን እንደተጻፈ አይታወቅም:: አርእስትም የለውም:: ይህን ጽሑፍ ያገኘሁት እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር በ2001 በሐምቡርግ ከተማ ነዋሪ ከሆነና ብርሃኑ ፈረደ ከሚባል ኢትዮጵያዊ ነው:: ጽሑፍ 33 ገጾች ያሉትና ለግጥሞቹ ከ1 እስከ 221 የሚል ተራ ቁጥር ተሰጥቷቸው የቀረበ ነው:: ሆኖም ግን ተራ ቁጥር አሰጣጡ ግልጽ አይመስልም:: ምክንያቱም በእያንዳንዱ ቁጥር ሥር የተጻፉት የግጥም ስንኞች እኩል አይደሉምና:: ዝቅተኛው ሁለት ከፍተኛው ደግሞ አሥራ አንድ የሚሆኑ ስንኞች ይገኙበታል::

ግጥሞቹ የቀረቡት በአማርኛ ቋንቋ ቢሆንም አንዳንድ የዓረብኛ ቃላትና ከእስልምና ሃይማኖት ጋር የተያያዙ አባባሎችና ጽንሰ ሀሳቦች ይገኛሉ:: አማርኛውም የወሎ ዘዬ ያለበት መሆኑ በግልጽ ይለያል:: በተጨማሪም ጽሑፉ በሁለት ሰዎች እንደተጻፈ ወይም እንደተገለበጠ ማወቅ ይቻላል:: የእጅ ጽሑፉን በኮምፒዩተር የጻፍሁት እንዳለ ነው፣ ምንም ሳልጨምር ሳልቀንስ:: ሆኖም ግን ዶክተር ኤሏ ፌኬ (EHESS, ፓሪስ) ተመሳሳይ ጽሑፍ እንዳገኘ ከገለጸልኝና እንድመለከተው ከላከልኝ በኋላ ሁለቱን የሼህ ሁሴን የግጥም ስብስቦች ለማነጻጸርና ለማመሳከር ሞክሬአለሁ:: ከአንዳንድ ስንኞችና ከአጻጻፍ ስልት በስተቀር በሁለቱ ስብስቦች መካከል የጎላ ልዩነት አላገኘሁም:: ብዙዎቹ ግጥሞች ተመሳሳይ ናቸው:: በብዛት ግን እኔ ያገነሁት ይበልጣል:: ከኤሏ ፌኬ የተለዩትን ወይምና በኔ ስብስብ ውስጥ ያገኘኋቸውን አዳዲስ ቃላት፣ ሐረጎች፣ ስንኞችና አንዳንዴም ሙሉ ግጥሞች በቀይ ቀለም ምልክት አድርጌባቸዋለሁ:: ይኸንን ስብስብ ከሌሎች ሰዎች ስብስብ ጋርም ማነጻጸር ይቻላል:: በመጨረሻም ወደፊት ተጨማሪ ጥናት ማድረግ ለሚፈልጉ ይጠቅማል በማለት የዋቤ መጻሕፍት ዝርዝር ቀርቧል:: የመጻሕፍቱ ዝርዝር ስለ አንዳንድ ታዋቂ ሼሆች፣ ስለ እስልምና ሃይማኖት እንዲሁም ስለእምነቱ በዓላዊ አከባበር በቃልግጥም ባህልና ትውፊት እንዴት እንደሚዜሙና እንደሚገጠሙ የመጠቆሙ ጠቃሚ ጽሑፎችንም አካቷል::

---

* ማሳሰቢያ ለአንባቢያን፣ የዚህ ጽሑፍ ጥናት ገና አልተጠናቀቀም። ሆኖም ግን የሼህ ሁሴንን ትንቢታዊ ግጥሞች ለማጥናትና ማነጻጸር፣ ወይም ግጥሞቹን ማንበብ ለሚፈልጉ ምሁራንና ተማሪዎች ጠቃሚ ይሆናል በማለት ለጊዜው በዚህ መልኩ እንዲወጣ ተደርጓል። ወደፊት ግን ጥናቱ ሙሉ በሙሉ ሲጠናቀቅ በሌላ መልክ ይቀርባል። በዚህ አጋጣሚ ገጣሚ አምሃ አስፋው በአማርኛ ቃልግጥም እና በኢትዮጵያ ፎክሎር ላይ ያዘጋጇኋቸውን መጣጥፎችና ጥናታዊ ጽሑፎች በራሱ ድረ ገጽ (**website**) ላይ ከሌሎች ምሁራን ሥራዎች ጋር እንዲወጡ ስለረዳኝ ከልብ አመሰግነዋለሁ። ጋሽ አምሃ ባማርኛ ቋንቋ፣ ለየት ያለ ያጻጻፍ ስልት ችሎታውን ያሳየ እና ታላቅ ገጣሚነቱን ያስመሰከረ ድንቅ ኢትዮጵያዊ ምሁር ነው።

## የሼህ ሁሴን ትንቢታዊ ግጥሞች

አንዳንድ ኢትዮጵያውያንና የውጭ አገር ጸሐፊዎች “የሼህ ሁሴን ትንቢታዊ ግጥሞች ናቸው“ እያሉ የሰበሰቡና በመጽሐፍ መልክ ያሳተሙ አሉ:: ለአብነት ያህል የሚከተሉት ይጠቀሳሉ:: አቶ ቦጋለ ተፈሪ በዙ በ1985 ዓ.ም *ትንቢተ ሸህ ሁሴን ጅብሪል* በሚል ርእስ አንድ መጽሐፍ አሳትመዋል[1]:: ዶክተር ኤሏ ፌኬ (2000?) ደግሞ አንድ መቶ ስልሳ ግጥሞች ያሉት የሸህ ሁሴንን ትንቢቶች ወደ ፈረንሳይኛ ተርጉሟል:: ኤሏ ያገኘው ቅጂ ከአቶ ዓሊ ይመር ሲሆን አርእስቱ “ትንቢተ ሼህ ሁሴን“ የሚል ነው:: በተጨማሪም በቅርቡ በ1996 ዓ.ም የታተመው የአቶ ጥላሁን ብርሃነ ሥላሴ ቤተ የታሪክ መጽሐፍ አንዳንድ የሼህ ሁሴን ጅብሪል ትንቢታዊ ግጥሞችን እንዳቀረበ መጥቀስ ያስፈልጋል::

የሼህ ሁሴን ትንቢታዊ ግጥሞች ከማኅበራዊ፥ ታሪካዊ፥ ፖለቲካዊና ሃይማኖታዊ ጠቀሜታ በተጨማሪ ያላቸው ባህላዊ፣ ፎክሎራዊና ሥነ ጥበባዊ ዋጋ እጅግ ከፍተኛ ነው:: ምናልባት ግጥሞቹ የሼህ ሁሴን ጅብሪል የራሳቸው ትንቢቶች ስለመሆናቸው በርግጠኝነት መናገር አይቻል ይሆናል:: ይሁን እንጂ የተለያዩ የታሪክ፣ የሥነቃልና የፎክሎር መረጃዎችን በመሰብሰብና በጥንቃቄ በማጥናት፣ ታዋቂ ሸሆችንና የእስልምና ሊቃውንትን በማነጋገር ግጥሞቹ በሼህ ሁሴን በቃል ስለመገጠማቸውና ከትውልድ ወደ ትውልድ በቃል ስለመተላለፋቸው በርግጠኝነት መናገር ይቻል ይሆናል:: ግጥሞቹ በወሎ ኅብረተሰብ ዘንድ በስፋት መታወቃቸውና ከትውልድ ወደ ትውልድ በቃል እየተላለፉ መተረካቸው፥ እንዲሁም መቼ፥ በማንና በምን አጋጣሚ እንደሚዜሙ፣ ታሪክን፥ ባህልን፥ ልማድንና እምነትን መሠረት ያደረጉ ክፍለ ሀገራዊ እምነታዊ፣ ፎክሎራዊና ታሪካዊ ሁናቴዎችን መመርመርና ማገናዘብ ስለሚቻል ነው::[2] እንደሚታወቀው ወሎ ውስጥ በርካታ የታወቁ ሼሆችና የእስልምና እምነት ማምለኪያ ቦታዎች ይገኛሉ:: ሕዝቡም በአብዛኛው ወደ ታዋቂ ሼሆች እየሄደ በጸሎት፣ በልዩ ልዩ ሃይማኖታዊ በዓላትና መጅሊሶች (ስብሰባዎች) ላይ እየተገኘ በተለይ በግጥም የሚባለውን መንዙማ የመስማት፣ አብሮ የማዜምና በቃል የማጥናት ባህሉ ከፍተኛ እንደሆነ በስፋት ይታወቃል:: በተጨማሪም በኢትዮጵያ ውስጥ ወሎ የግጥም፥ የዜማ፥ የዘፈንና የልዩ ልዩ ባህላዊ ጨዋታዎች ምንጭና መሠረት መሆኑ የታወቀ ነው::

እስካሁን የታተሙትን ሥራዎች ስንመረምር፣ በአቶ ቦጋለ ተፈሪ መጽሐፍ ውስጥ 117 ግጥሞች ከትንታኔ ጋር ቀርበዋል:: በትንታኔው ውሰጥ ከቀረቡት መካከል:- ስለ አጼ ዮሐንስ 21፣ ስለ ሙሐመድ አሊ 30፣ ስለተፈሪ (መኮንን) 22 ግጥሞች ትንታኔ ተደርጎባቸዋል:: በተጨማሪም በጣም ብዙ ግጥሞች በፊደል ተራ ያለ ትንታኔ ተጽፈዋል:: ቀጥሎም እንደዚሁ በርካታ ግጥሞች ከአንዳንድ አጫጭር ማብራሪያዎች ጋር ቀርበዋል:: ከዚህ መጽሐፍ በፊት የሼህ ሁሴንን ትንቢታዊ ግጥሞች በተመለከተ ምንም መጽሐፍም ሆነ መጣጥፍ እንዳልታተመ ደራሲው በመግቢያቸው ላይ ጠቅሰዋል:: መጽሐፉ ስለ ወሎ ክፍለ ሀገር ታሪክ ባጭሩ የዳሰሰ ሲሆን፣ የሼህ ሁሴንን የሕይወት ታሪክም አቅርቧል:: በዶክተር ኤሏ ፌኬ (EHESS, ፓሪስ) ጥናት ውስጥ ደግሞ 116 ግጥሞች ወደ ፈረንሳይኛ ተተርጉመው ቀርበዋል:: ፌኬ የሰበሰባቸው ግጥሞች አጭር መግቢያ በአረብኛ ቋንቋ ያላቸው ሲሆን የአቶ ዓሊ ይመር ቅጂ (ቨርሲዮን) እንደሆነም ጠቅሷል:: ኤሏ ፌኬ ለግጥሞቹ አንዳንድ አጫጭር ማብራሪያዎች በግርጌ ማስታዎሻ ሥር ከመስጠቱ በስተቀር ሰፋ ያለ ትንታኔ ወይም ማብራሪያ አላደረገም:: የፌኬ የትርጉም ሥራ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ አልታተመም ነበር::

---

[1] ቦጋለ ተፈሪ፣ 1980 ዓ.ም፣ ሼህ ሁሴን ጅብሪልና ግጥሞቻቸው። ያልታተመ፣ ለባችለር ዲግሪ ማሚያ የቀረበ ጥናት። የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ክፍል፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ።

[2] ይኸን በተመለከተ በተለይ የሁሴን አህመድን (2002)ና የብርሃኑ ገበየሁን (1998) ሥራዎች ይመልከቱ።

ምንም እንኳ አሁን የተገኘው የግጥም ስብስብ ልዩ ልዩ ታሪክ ያለው ቢሆንም አቀራረቡ የኢትዮጵያን ታሪክ በዘመናት ቅደም ተከተል በትክክል የሚተርክ አይመስልም:: አንዳንድ ጊዜ ስለ እስልምና ሃይማኖትና ስለ ትንቢቱ ተናጋሪ የግል ሁኔታ ይተርካል:: ቀጥሎም ታሪኩን ከዘመን፣ ከነገሥታት ፖለቲካዊና አስተዳደራዊ ሁኔታዎች (ለምሳሌ፥ አጼ ቴዎድሮስ፣ አጼ ዮሐንስ፥ አጼ ምኒልክ፥ እቴጌ ጣይቱ፥ ልጅ ኢያሱ፥ ንግሥት ዘውዲቱ፥ ተፈሪ፣ አጼ ኃይለ ሥላሴ፣ ደርግ፣ ወዘተ.) ጋር የተያያዙ በርካታ ጉዳዮችን በስፋት ይገልጻል:: ግጥሞቹ ከአጼ ዮሐንስ አራተኛ ጀምሮ እስከ ወታደራዊ ደርግ አገዛዝ መጨረሻ፥ ምናልባትም አሁን እስካለንበት ኢሕአዴግ ዘመን ድረስ ያለውን የኢትዮጵያ ታሪክ በትንቢታዊ ትረካ መልክ የሚያቀርቡ ናቸው:: ግጥሞቹ በተለይ ለታሪክ፣ ለቋንቋ፣ ለሥነ ጽሑፍ፣ ለፎክሎርና ለአንትሮፖሎጂ (ሥነ ሰብእ) ተማሪዎችና አጥኚዎች ከፍተኛ ጠቀሜታ እንደሚኖራቸው አያጠራጥርም:: የግጥሞቹ የቋንቋ አጠቃቀም የወሎን አማርኛ ለማጥናትና ከአረብኛ የተወሰዱ የተለያዩ የውሰት ቃላትን ለመመርመር ባያሌው ይረዳል:: የቃላቱ አመራረጥ፣ ተምሳሌታዊ አገላለጾችና ዘያዊ አባባሎች ክፍለ ሀገራዊ አሻራቸውን የጠበቁ ለመሆናቸው በጣም ጥሩ ማስረጃዎች ናቸው::

ለመሆኑ ትንቢቱን ተናገሩት ወይም ግጥሙን ገጠሙት ወይም አዜሙት የሚባሉት ሼህ ሁሴን ጅብሪል ማን ናቸው? በርግጥ ሰውዬው በሕይወት የኖሩ ናቸው? ወይስ በአፈ ታሪክ ወይም በፈጠራ የሚታወቁ ሰው ናቸው? ግጥሞቹንስ ራሳቸው ስለመግጠማቸው ማረጋገጥ ይቻላልን? የወሎ ሕዝብስ ሙስሊሙም ሆነ ክርስቲያኑ፥ ወንዱም ሆነ ሴቱ፥ ልጁም ሆነ አዋቂው፥ የተማሪውም ሆነ ያልተማረው፥ የከተማውም ሆነ የገጠሩ ኅብረተሰብ ስለ ሼህ ሁሴን ጅብሪል ምን ያውቃል? ምን ይላል? እነዚህንና ሌሎች ጥያቄዎች አንሥቶ በስፋት መወያየት ይቻላል:: ለጊዜው የዚህ ጽሑፍ ዓላማ የግጥሞቹን ይዘት ከታሪክ፣ ከሥነ ቃልና ከባህል አኳያ መተንተንና ማብራራት ቢሆንም፥ ወደፊት ሰፋ ባለ ጥናት ከላይ የተነሡትን ጥያቄዎች ለመመለስ እንሞክራለን:: እግረ መንገዳችንን ግን የሼህ ሁሴን ጅብሪልን የሕይወት ታሪክ ባጭሩ እንመለከታለን::

## የሼህ ሁሴን ጅብሪል አጭር የሕይወት ታሪክ

ሼህ ሁሴን ጅብሪል ከ1811- 1908 እንደኖሩ ጥላሁን ብርሃነ ሥላሴ ቤተ (1996፣ vii) በመጽሐፋቸው ጠቅሰዋል። ስለ ሸህ ሁሴን ጅብሪል የሕይወት ታሪክ በስፋት የጻፈ ቦጋለ ተፈሪ በዙ ነው:: አቶ ቦጋለ ተፈሪ ፣ ሼህ ሁሴን ጅብሪል ከአባታቸው ከሼህ ጅብሪል በወሎ ክፍለ ሀገር በወረሂመኖ አውራጃ፣ በባዙራ ምክትል በባሆች ቀበሌ፣ ልዩ ስሙ እምበለ ሴዳ ተብሎ በሚጠራ ቦታ በ1811 ገደማ ተወልደው በ97 ዓመታቸው አንዳረፉ ጽፈዋል:: አባታቸው በዘመኑ በቃሉ አውራጃ ታዋቂ ለነበሩት ለገታው ሼህ ቡሽራ አድረው ለሰላሣ ዓመታት በመውሪድነት አገልግለዋል:: (1985፣ 21) ጌታው ሼህ ሁሴን መፍረ የጀመሩት ገና በሰባት ዓመታቸው እንደሆነና የሚናገሩትም መሬት ጠብ እንደማይል ተጽፏል:: አሐዱ ወይም ቢስሚላሂ ብለው ፍርድ የጀመሩት በአጼ ዮሐንስና በመምሬ ግርማ በተባሉ ቄስ ነው ይባላል። እየታወቁ ሲመጡ ወደፊት የሚሆነውንና የሚመጣውን ከነመፍትሔው መናገራቸውና መተንበያቸው ነበር:: የሚናገሩትም በግጥም ነበር። ከዚያ ነገሥታቱም፣ መሳፍንቱም፣ ትንሹም ትልቁም እሳቸውን መጀን ማሌት ያዘ። (1985፣ 24)

ግጥሞቻቸውን ከእረኛ እስከ ቃዲ ያውቀዋል፣ይለዋል:: ሼህ ሁሴን የነቢዩ መሐመድ ተከታይ ነበሩ:: ቢሆኑም እንደ እስላሞች ጫት አይቅሙም፣ ሶላት አያደርሱም፣ መስገጃ ቁርበት፣ ውኃ መያዣ ጠሴ አያንጠለጥሉም:: እንደ ዓባይ ጠንቋይም መጽሐፍ አይገልጡም፣ ጠጠር አይጥሉም:: ግን ሱረት (ሐቀኑር) ያሸታሉ፣ ብርዝ ይጠጣሉ፣ ፍርድም ሲፈርዱ ማለት የሚታያቸውን ሲናገሩ ብርዝ በፎሌ (በሸክና) ይዘው ነበር ይባላል:: (1985፣ 25) በሕይወት ዘመናቸው በጊዜው ታዋቂ ከነበሩት ባለዐቢ ከጥቅሳው ሼህ፣ ወልይና አሊም ጋር

ተጣልተውና ተቃቅረው እንደነበር፣ ወዲያውም በጠና ታመው እንደነበር አቶ ቦጋለ ጠቅሰዋል። (፣ 25) ከጥቅሳው ሼህ ጋር ጠባቸው ይፋ ከሆነ ጀምሮ በሽታቸው ጠናባቸው፣ እናም የሚከተለውን ግጥም አዜሙ ይባላል፣

በጎጃም፣ በትግሬ፣ በሸዋ፣ በጎደር ሳገሳ ሳገሳ
ስብርብር አረገኝ የጥቅሳ አንበሳ። (፣26)

## የሼህ ሁሴን ጅብሪል ትንቢታዊ ግጥሞች

1. ዋርዳው መጣና ቆይ አለኝ አንድ ዓመት
ጫትክን እየበላህ ሳታድር ከሴት
አምሬን እየሞላህ ጠጅን ሳታሸት
ደረሳህን ይዘህ ሳትወጣ ከቤት
እኔም ኸልዋ ገባሁ ቆየሁ አንድ ዓመት::

2. አንድ ዓመት ጫት ቅመን ዓለሙን ስንድር
ንጉሥ እየፈራኝ ሳይጠላኝ አሽከር
ወዲያው ስሜ ታውቆ ሸዋና ሐረር
እኔም በመስታወት ዓይኔን ሳሳምር
ቃሌ ሳይዛነፍ ሳልደናገር::

3. አላህ ሲያሳምረው ሰው እጣው ሲወጣ
ዓመት አስቀመጠኝ ከኸለዋ ሳልወጣ
ወዲያው መናም አየሁ አንበሳ ሲወጣ
ነብር እየመራኝ ጅብ ከፊቴ መጣ
ግመል ተሸክሞኝ የሆነ መላጣ::

4. መናቡ አይቼ ለሰው ሳላወራ
በሰባተኛው ቀን መጣ አንድ ቀብራራ
መሰንቆና ዋሽንት በእጁ ይዞ ጭራ
ከኔ ጋራ አደረ ጫት ሲቅም ሲያወራ
መሰንቆ እየመታ ሲዘፍን ሲያቅራራ::

5. አላህ ሲያሳድገው ነገሩ ሲሰላ
በስምንተኛው ቀን ጫት ስንቅም ስንበላ
ድቤ ተሸክሞ መጣ አንድ ሻንቅላ
ጫት በጨርቅ ይዞ ጠጅ በሸክላ
ሁሴን ቡን አፍላልኝ ነገሩ እንዲሰላ::

6. ስምንት ቀን ከደምኩ ሳትናገር አፌ
የቤቴን ግድግዳ ግንዱን ተደግፌ
ፊቴን እያጠብኩኝ እንዳይመጣ እንቅልፌ
እንዲቀመጡበት ጋቢዬን አንጥፌ
አይገርማችሁም ወይ ሳልነግድ ማትረፌ::

7. መናውን ፈሰርነው አንተ ሳትናገር
ድቤውም ዋሽንቱም መሰንቆው ጭራ አይቀር
ጠጅና ጉማሬ ጫት ስንቅም እንደምር
ጀባ ብለንሃል በዚሂር መነጸር
ሐሲድ የሚመታ አንድ እንኩዋን ሹም ሳይቀር::
8. አላህ ካደረገን የሽልቁ ወዳጅ
በድቤና በጫት ልጀምር በጠጅ::
መሰንቆ እየመታሁ ልወዝወዘው እንጅ
በጭራ በዋሽንት ሰው ባልነካው እጅ
አውሊያ እምጠራበት ሶላት ሳልሰለች::

9. ጫት ባፋችን ይዘን ጠጅ እየጠጣን
ጥቁር ጭራ ይዘን ድቤ እየመታን
ሐሲድ እንዳይነካን አውሊያ እየጠራን
አምስት አውቃት ሶላት እየሰጋገድን
ሰው ያልነካው እቃ ጀሊሉ ሰጠን::

10. መጪውን አየነው ጉድ አጃኢበት
ዓለም ስትስቅብኝ እኔ ሳቅኩባት
ለአዳም መህሉቃት ከወንድም ከሴት
ካለቁት በስተቀር ያሉት በሐያት
ተከትቦ አየዋለሁ ስሙን ወደፊት::

11. ስሙን ይነግረኛል ዋሪዳው ሳይስት
ገና በእናቱ ሆድ ሳሽለቅ ፊት
ለወልይ ለንጉሥ፣ ለራስ መሳፍንት
ምን አስለፈለፈኝ ሊታይ ወደፊት
እኔም በል ብሎኝ ነው የምወሽክት::

12. ሃምሳ ዓመት ስናገር ሰምተው ጉድ እያሉ
እንደ ፍልፈል አፈር ሰው ሲፈለፍሉ
(ሰምተው እንዳልሰሙ አላየንም አሉ
እንደ ፍልፈል አፈር ሰው ሲፈለፍሉ)
እኛም ሰደድናቸው ከአፈር እንዲተሉ
ቀሩ እንደፈራነው ውሽታም እንዳይሉ::

13. ሃምሳ ዓመት ከደመኝ መሐመድ ኑር ዒሳ
መድና ወረቀት ከእጁ ሳይነሣ
ይከትበው ነበረ ዋሪዳው ሲነሣ
የፈረድኩትን አንድ ቀን ሳይረሳ
መጪውን ፈርጃለሁ ዓለም እስቲከሳ::

14. ቃሊቾችም ጠሉኝ ጠጅ ይጠጣል ብለው
ደብተራውም ጠላኝ ሹም ተጠጋው ብሎ
ባለዛሩም ጠላኝ ሰው ሂደበት ብሎ
ፋቅራውም ተጠጋኝ ምን ይፈርዳል ብሎ
እኒህን ችዬ ነው የሰጠኝ ጀሊሉ::

15. ጀግና አጼ ዮሐንስ ያበሶች ወንድም
የዛሬን ማርልኝ ያለ ዛሬ አይለምድም
በነገረ ሠሪ ሰው አይታረድም
እንዲህ ከሆነማ አንድ ስው አይተርፍም
እየደነገጡ ይሄዳሉ የትም::

16. ዓባይ በጣና ላይ መሄዱ ለምን ነው?
ትንሹ ሲያጠፋ ትልቁ ሊችል ነው፣
ቢያከፋም ቢያበጅም ዓባይ ማለፉ ነው
ሰውን በግዴታ የሚገዛው ማነው?
ከምክር በስተቀር የቀረው ከንቱ ነው::

17. ማረዱ ከፋ እንጅ ጀግንነት አያጣም
እስላም እሚያርድ እንጅ እሚወድ አይመጣም፣
የፈራህ ሰው ወጣ እኔ መልስ አላጣም
ይዘገያል እንጅ ሰው የጁን አያጣም
መተማ ከሄደ ተመልሶ አይመጣም::

18. አንተም እድሜህ አጭር ወይ ዘርህ አይገዛ
(ኀርፍ ደርሶ አይወስድም አለቅጥ ካልበዛ)
እንጨት ከደረቀ ቢቀቡት አይወዛ
(ሐበሻ ክፉ ነው አይምሰልህ ዋዛ)
መተማ እስቲጠራህ በብልሃት ግዛ::

19. እመክርህ ነበረ መች እሺ ትላለህ
ሀሳብህ ብዙ ነው መንገድ ታበዛለህ
መተማ ለመዝመት አሁን ትሄዳለህ
(መመልስክን እንጃ እዛው ትቀራለህ)
በድርቡሽ ጎራዴ ራስህን ታጣለህ::

20. አንድ ዓመት ሲቀረው ምኒልክ ሊነግሥ
አላህ መተማ ላይ ይስላል መቀስ
በደም አጨማልቃ የምትቆራርስ
እራስ የምትቆርጥ ያውም የንጉሥ
አንደዜ ተመታች የማታላውስ::

21. አራት ወር ሲቀረው ምኒልክ ሊነግሥ
በመተማ በኩል ትጨሳች ጭስ
ጭሷ በራስ ገብታ (የምታስነጥስ) ትጨርሳለች ጭስ
እጅግም አትበጀው ለአጼ ዮሐንስ
አላህ ሸቶበታል አንገቱን ሊቀምስ::

22. እውቀትም የላቸው አሉን ጥንብ እርኩስ
ብለው ሰደቡን ደብተራና ቄስ
ሂጄ ልናገረው ለአጼ ዮሐንስ
ፈርጀለት ነበር መቅደላ ሲፈርስ
እንዴት የነቢ አሽከር ይሆናል እርኩስ?

23. የሰማም ያልሰማም ያልቅስ
መች እኔ እፈራለሁ ደብተራና ቄስ
መተማን ድል አድርጎ እሱ ቢመለስ
እንግዲህ የኔ ጫት ጥንብ ናት እርኩስ?
መተማ ካልሄደ እኔም ጫት አልቀምስ::

24. ጦሩን አስከትሎ መተማ ሲደርስ
ከበቅሎው ወረደ አጼ ዮሐንስ
የጦሩን መከታ ጋሻውን ሊለብስ
እሱ እራሱን አጥቶ ሰውን ሊያስጨርስ
በጥረት አይድንም ጥፋ ያለው ነፍስ::

25. እንዴት በገዛ እጁ ሞት ይመኛል ሰው?
መተማ አትሂድ ብዬ ብመክረው
መቸ ይመለሳል ያዘዘበት ሰው
(ደም እየሸተተው ሞት እየጠራው
እንዴት ሰው ለአንገቱ አያዝንም ወይ ሰው)

26. ፈረሱን ጫጭነው ድርቡሾች ዘለቁ
ኸሊፋና ዑመር ድባጢን ዘለቁ
ከዚያም ከዚህ ያሉት ተደበላለቁ
ዮሐንስ ከጭፍራው ፈርተው ተጨነቁ
የሚያስታርቅ ጠፍቶ ስንት ሰው አለቁ::

27. የአህያ ልጅ በቅሎ በብር ተሸልማ
ዮሐንስን ይዛ ወረደች መተማ
ከጌታዋ ራስ ጋር በቁም ልትቀማ
ስንቱን ሰው ፈረጀው ደጉ አገር መተማ
ስንቱን አርዶት ነበር እስላም እንዳይለማ::

28. ምኒልክ ደስ አለው ምጡን ሲፈረጅ
እኔም ጫት በመቃም ነጀ ወጣሁ እንጅ
እስላምን የሚወድ ወደፊት ይምጣ እንጅ
ዮሐንስ ክፉ ነው የለውም ወዳጅ
መተማ ደጉ አገር ገላገለን እንጅ::

አላህ ገላገለን በዟሂር መከራ
እንግዲህ ምኒልክ አይዞህ እንዳትፈራ
ዮሐንስ ሊሄድ ነው ጦሩን እየመራ
ማረድ የለመደ መቼም ሞት አይፈራ::
ሞቱ ብላሽ ሆነ እንዲህ ሲንጠራራ::

29. አንተም ጨካኝ ነበርክ ጨካኝ ወረደብህ
እንደ ፍሪዳ ላም በቁምህ አረዱህ
በቅሎና ገጧ ጋር በቁሟ ማረኩህ
እራስክን ቋንጣ አርገው ሥዕል አደረጉህ
አላፊው አግዳሚው እንዲሰደድብህ::

30. አልሐምዱሊላሂ ለዚህ አበቃህ
ዮሐንስ እራስህን በችንካር መቱህ
አላፊው አግዳሚው እስቲተፋብህ
ሰው የጁን አያጣም እንዲህ አረጉህ
የወሎን መሻኢህ እያረድክ ሰቅለህ::

31. አጠቋቆራቸው ከሰል ይመስላሉ
ከመሕሉቁ ብሰው በጣም ይጠቁራሉ
መተማን ድል አርገው ጎንደር ይገባሉ
ደቆራና ዳይንት ብዙ ሰው ያርዳሉ
ከሺህ ታቦት በላይ በእሳት ያነዳሉ::

32. ማረድ ተጀምሮ ድራና ፎገራ
ምን ይበጀው ይሆን የጎንደር አማራ?
አይተኸው የማታውቅ መጣብህ መከራ
ብዙ ሰው ይጠፋል ካልሰለመ አማራ
ይለበልበዋል ያርደዋል በካራ::

33. ወደ ሱዳን አገር ዋሪዳው ካመራ
ደፈረኝ ካልሉ ሳዳቶችን ልጥራ
አሁን ድረሱልኝ ይዞኛል ደብተራ
ወትሮም የመሐዲ ዘር አስላችሁ አይኮራ
ገላገላችሁኝ አልቅሼ ብጣራ::
34. ቢደፍሯቸው እዳ ዝም ብል ችግር
ዋሪዳው መጣና አለኝ ተናገር፣
እንግሊዝ ከሱዳን ካልለቀቀ አገር
ይዘገያል እንጅ ኋላ አለ ነገር
መሕዲ ዘር ባለቃ ሲል ደንገር ደንገር::

ሱዳን ብሎ ማለት ተፍሲሩ ሻንቅላ
(ከነሱ ካልሆነ አይጋቡም ሌላ
መጠጥ ይወዳሉ ሐራራም አይጠላ)
ዘራቸው ልዩ ነው ናቸው የአላህ ሰባት በላ
ሰባት ቋንቋ አላቸው ሁሉም በጠቅላላ::

35. የሱዳንን ነገር በስንቱ ላውሳቸው
ካላስፈነደዱ ፈርጅም አይመስላቸው
ከእኛም ሰው አይተፋ ነጭ ያስተማራቸው
የወንዱስ መላ አልቋል ሴቱ አላህ ያብጀው
ስንቡል እያጠበች ገልባ ከሰጠችው::

36. ድርቡሽና ሱዳን መልካቸው ጥቁር ነው
አገሩ አንድ ቢሆን ቋንቋው እየቅል ነው
ጥንቱም ፍጥረታቸው ዘራቸው ልዩ ነው
በዟሂር ሲጠሩ ስማቸው እስላም ነው
ቸርነት አያጡም እጃቸው ለጋስ ነው::

37. ድርቡሽ ጥሩ እስላም ልባቸው የጠራ

ሶላትን አይተውም ቢበዛበት ሥራ
ችግርም ቢገጥመው ይችላል መከራ
አገራቸው ሜዳ የለውም ተራራ
ልብሳቸው ቀሚስ ነው የለውም ዳኢም ታጥቀው ሥራ::

38. ከእኔ ተመርቀው ሴት ልጅ ከወለዱ
ለጉግሳ ይዳሯት እንዳትዛመዱ
ሌላም አያገባት ፈርዶታል ዘመዱ
እንግዲህ እሜቴ ጫት ቃሚን ይውደዱ
አሁን ነው መሸመት ደጎቹ ሳይሄዱ::

39. በአዳራሹ ገብተህ በእልፍኙ ላይ ውጣ
በእልፍኙ ላይ ገብተህ በአዳራሹ ውጣ
እንደምንም ብለህ ሸዋረጋን አምጣ
የተያዝከ እንደሆን እኔ በጉድ ልውጣ
እኔ ፈርጃለሁ ሌላ እንዳታመጣ::
ወንድ ትወልዳለች ግን የለውም ዕጣ::

40. በራስህ ገብቼ በሆድህ ብወጣ
ከትርንጎ በቀር ሌላ ምንም ታጣ
ይኸ ያልሆነ እንደሁ እኔ በጉድ ልውጣ
ሆድህን የሚገልጥ ሽማግሌ ይምጣ
ይኸንን ጉድ ሳላይ ከቤትም አልወጣ::

41. ተው አቶ ሙቀጫ እኔን አታላግጣ
ጌሾና ቡናህን ውጣና ቀጥቅጣ፣
በሽታም እንደሆንክ እኔ በጉድ ልውጣ
ማንን ታሞኛለህ እኔ አልወድም ላግጣ
እኔ እሳት አልገባም ነግረንሃል ቁርጣ::

42. ምኒልክ ክፉ ነው በስንቱ ፈተነኝ
እንድአለፋት ጠንቋይ በእሳት ሊያቃጥለኝ
በሰው እጅ አልጠፋም አላህ ካልገደለኝ
እንኳን ከመምሬ ፊት አላህ ሊቅ አረገኝ
እፈራው ነበረ በጅኑ እንዳይጠልፈኝ::

43. የምኒልክ ጠንቋይ ዋና ደብተራው
ያስፈጨው ነበረ ጅኑን እንደ ሰው
በርበሬ ነበረ የሚቋደሰው
ጅኑን እየላከ ስንቱን ሰው ፈጀው
መምሬ ሐሲድ ነው ከመጀመሪያው::

44. እንግዲህ ወንድሜ ስማኝ የኔን ፍርድ
መውለድህ አይቀርም ከጭን ከገረድ
ቁርአን የሚቀራ ኢልምን የሚወድ
መጨረሻው ከፍሮ ካልሆነ ፈሳድ::

45. ቴዎድሮስ ለጋሥ ሰው ነው ቸርነት አያጣም

ዘሩም ደጎና ሰው ነው ቢገጥም አይወጋም
ማንም ያሞኘዋል ያሳዝናል በጣም
ለሰውም ደጎና ነው እስላምን አይጎዳም
እራቅ ይላል እንጅ የእስላም ዘር አያጣም::

ዮሐንስ ንፉግ ነው ሰው ቢበላ አይወድም
የሰው ያየ ጊዜ ያደርጋል ጉድምድም
ሆዱም ለብቻው ነው ሰው አያስቀርብም
ለጦር ግን ጀግና ነው ቢሄድ አይታክትም::

46. የጠንቋይ ውዴታ ፍቅር ይቅርብህ
ለአንተ ሲህር አያጣም ይኸው ነገርኩህ
ቢያጣ አርን አያጣም እንዳይጥልብህ
ስታልፍ እንድትረግጠው ሰው እንዲስድብህ
አሩ ይሸታል ብለው ሰው እንዳይቀርብህ::

47. አሥር ዓመት ብችል ሊያርዱኝ ተሰለፉ
ለካስ ለዚህ ነውይ እምቢ ያለኝ እንቅልፉ
ለአላህ ትቼው ነበር በዱኒያ እንዲያልፉ
እንግዲህ ዘላለም መሬትን ይቀፉ
በቶሎ ገላግለኝ ሰው እንዳያለፉ::

48. በእነ ቀለመወርቅ ነሱር ባላገኝ
በመምሬ ጉርሙ ነሱር ባላገኝ
በእነ አለቃ ሣህሉ ነሱር ባላገኝ
በእነ አለቃ ውብነህ ነሱር ባላገኝ
እኒህ ተዋርደው ነው ንጉሥ የፈራኝ::

49. በእለቃ ቀለመወርቅ ነሱር ባላገኝ
በእነ ይመር አደም ነሱርን ባላገኝ
በእነ አለቃ እዮብ ነሱር ባላገኝ
(በአውገረድ አለማሸ ነስሩን ባላገኝ)
ችለን ሰደድናቸው እንቅልፍ ቢነሱኝ::

50. ነግሬአቸው ነበር ፊት ሳልታመም
አሁንም አየሁት አላህ ሲፈርም
አፈሩን በጥብጦ በጥቁር ቀለም
ቃልቻ ይኸን ፈሥር እንዳትታመም
በቀር ትጓዛለህ አምተህ ሳትሰልም::

51. አላማጣን አልፈህ ማይጨው ትዘምታለህ
ነጭ አሥመራ መጥቶ አድዋ ትገጥማለህ
አድዋን እንዳያልፍ በጣም ትዋጋለህ
ጦርህ ግን ያልቃሉ ድል ግን ታደርጋለህ
በመከርኩህ ምክር ነጃ ትወጣለህ::

52. የሸዋረጋ እናት ሐለቴን ያውቃሉ

ሁሴን መጣ ሲባል ጋንዎን ያጥባሉ
ቁጠማ ጎዝጉዘው አዱርስ ያቀርባሉ
ደስ ደስ እያለዎት በጣም ይስቃሉ
መጋረጃ ጋርደው ቁጭ ብለው ያድራሉ::

53. መምጣቴን ሰምተው ልደር ካሉ ቄሱ
ሐለቴን ያውቃሉ ጣይቱን ያስታውሱ
አዱርስ ጨሰ ብለው እንዳይወሰውሱ
ጫት በአፋችን ከያዝን ጠጅን እንዳቀምሱ
ዋሪዳው ይማታል አይወድም መጅሊሱ::

54. የነብስ አባትዎ ከሆኑ እኚህ ቄስ
ቁጭ ብለው ይደሩ ከእኛ ጋር መጅሊስ
መውደድስ አትወዱም ጳጳስና ቄስ
ግን ለአጼ ምኒልክ እንዲላቸው ደስ
ሰው ዝም ብሎ ያድራል እንኳን ሊደግስ::

55. አርባ ጊዜ መጣሁ የልብህ ይድረስ
ፌትም ዱአ አርገናል አንተ እንድትነግ፣
ቀልብህ ደኅና ቢሆን ብትወድ መጅሊስ
ገርፌህ ባትሰቅል እንደ ዮሐንስ
ስንቱ እስላም ወደደህ ሁሉን አለው ደስ::

56. ጎጃም ተክለ ሃይማኖት ጎንደር እራስ ተሰማ
(ትግራይ እነ ራስ አሉላ አባ ጅፋር ጅማ
ሐረር ራስ መኮንን ዘራቸው የገማ
እኔ ተናገርኩኝ ያልሰማህም ስማ
ከጉግሣ ዘር በቀር የለም የሚለማ::

57. መች ባንተ ይሆናል ምኒልክ ንጉሡ (60)
አንተ አስበህ ነበር ልትሰጥ ለእያሱ
እንኳን ሊነግሥና ይያዛል ለራሱ
በራስ መኮንን እጅ ትጠፋለች ነብሱ
ከጌታ ተፈርዷል አርደውት ሊነግሥ::

58. ከገረድ ተወልዶ እደግ ብንለው
ጥንብ አቀረበልን እዩት ይህን ሰው
ከሸዋረጋ ፊት አሁን ላዋርደው
ልልክበት ነበር ዳግሚያ እንዳይለምደው
አይለምደውም ነበር ቄስ ወርቁን ቢያየው።

59. ወይ መሐመድ አሊ ምን ሆኗል ይኸ ሰው
በድየው እንደሆን ልጠየቅ በሰው
በዮሐንስ ጠበል ዲኑን ሲያረክሰው
ጥፋት በእሱ ሆኖ ተገኘበት ይህ ሰው
ኋላ ብትሞት ማነው የሚዋሰው?

60. ጠጅና ሥጋህን ከፊቴ ላይ አንሣ
እኔ በበሬ ሽንጥ ሰውነቴ አይሳሳ
በአንድ ቀን ተርቤ ሰውነቴ አይከሳ
አላህ የጠላውን አልበላም ነጃሳ
ወንዝ ለወንዝ ሄጄ እበላለሁ ዓሣ::

61. አንተ ብታፈቅረኝ እኔ ብወድህ
አትቆጣም ብዬ እኔም አንተ አልኩህ
እንዳይደነግጡ የነብስ አባትህ
ከመጅሊስ ካልሆነ እኔም አልደፍርህ
አንተስ ምን ትስተው እኔ ባልነግርህ?

62. አባቱ (መተማ) ሄዶ አፈር ሊቀምስ
ልጁ ኋላ ቀርቶ መስሎት የሚነግሥ
እንኳን የልጅ ልጁ እራሱም አይነግሥ
በአዙል ተፈርዷል ምኒልክ ሊነግሥ
አስቦ ነበረ በሁለት ሊነግሥ::

63. እኔ በሚካኤል ደንግጨ አልታመም
ኢልሙም ከንቱ ይሁን የቀረው ዘላዓለም
እንዲህ ሊያጋልጠው ዲኑንም ሊዘ(ዞ)ልም
ነግሬው ነበረ ግን ነገሬ አይጥምም፣
አውጥቻለሁ ጣሉ ይህ አህያ አይድንም::

64. ምኒልክ አሥመራን ለነጭ ከሸጣት
ይዘገያል እንጅ ይመጣል ፍጅት፣
ስንቱ ይዋረዳል ከወንድም ከሴት
ሸዋ የዚያን ጊዜ የለውም ዕረፍት
ቀጥሎ ይነዳል የጀርባው እሳት::

65. እንኳን ለኢያሱና ሳይታይ አባቱ
ምን ብለናት ነብር ትመስክር እናቱ
እስከሚሞት ድረስ ኋላ ባሚሟቱ፣
ደግሞ አጼ ዮሐንስ መተማ ሳይዘምቱ
ትዝ አይላችሁም ወይ በጫት የማልኩቱ::

66. ክፉ ዱላ አለን የማይምር ለዕለት
እስተውሎ የሚመታ በሩቅ የማይስት
እኔ ሹም አልፈራም ጉድ ካየሁበት
እንዴት ጥንብ ሰጡኝ አያውቅም መስሎት
ማነው ያሳሳተው ያደለው እሳት።

67. ስክሮ ካልወደቀ አያራም ከቤት
ዛፍ ካልተቆረጠ አይወድቅም እመሬት
ሴት ፈርጂን ካልሡፋች የባሏን ንብረት፣
ኢያሱ አደብ ግዛ እንዳትሳሳት
ቆጥረህ ድረስበት መነን ምንህ ናት?

68. ሚካኤል ተው ተብት በኩፍር ሳትቀጣ
ይበቃሃል የሚል ከአላህ አዋጅ መጣ
እንዴት ያለች ንፋስ የሆነች ባላንጣ
በጥፊ ብትመታው በአፍንጫው ደም መጣ
ጉዞው ተቃረበ እሩሁ ልትወጣ::

69. ጉግሣና ራስ (ወ)ሎሌ፣ አጼ ዮሐንስ
ሚካኤል፣ ምኒልክና አጼ ቴዎድሮስ
ዘውዲቱና ፈረንጅ ተፈሪ ድረስ
በብልሃት ገዟት አልጋው እንዳይፈርስ
መጨረሻው ከፍቶ ጣሉት እንደርኩስ::

70. የአላህን ትተው በውሻ የሚመሩ
በሐበሻ መሬት ግፍን የሚሠሩ
ቁመታቸው አጭር መልካቸው የሚያምሩ
አይነግሡም ብላችሁ አትወዳደሩ
ሃምሳ ዓመት ይነግሣል እግረ ውትርትሩ::

71. ባሕር ወዲያ ማዶ ዘር መጣ ሊጠቅም
ግድግዳው የሚያምር በሽንጥ የሚጠቅም
ቅጠሉ ለስላሳ ቁመቱ ረዣዥም
እሱን ያልተከለ እንዴት ይለጅም
ሸዋ በተለየ ያለሱ አይቆምም::

72. ሥራቸው ባለጌ አህያ የሚበሉ
ባሕር ወዲያ ማዶ ክፉ ሰዎች አሉ፣
ሐበሻን ለመውረር ሐሳብ ያስባሉ
የኋላ የኋላ መምጣት ይመጣሉ
አምስት ዓመት ገዝተው ወዲያው ይሄዳሉ::

73. ድንጋይ ዱቄት አርገው መንገድ የሚያበጁ
ገመድን ዘርግተው መብራት የሚያበጁ
አህያ የሚያርዱ አሞራ የሚፈጁ
መጡ እየተማሩ ሐበሻን ሊያበጁ
ማማሩን አማረች ግን ብዙ ሰው ፈጁ::

74. እግሩ እንደ ሙቀጫ የሚንከባለል
ቢሄድ አይታክተው አቀበት ቁልቁል
ጭቃ ካለው መንገድ መሄድ የማይችል
ገደል የሚያንሸራትተው የሚንከባለል
ይህንን የገዛ ካለፈው ምንም አይል::

75. በገዛ እጁ ነድፎ ፈትሎ የሚሠራ
ሰውን የሚያስገርም የሚሠራው ሥራ
ልብሱ ተፈላጊ ሰውን የሚያኮራ
ልብሱን ላይሸከሽክ አስተውሎ የሚሠራ
በዚህ አይግረምህ ሌላ አለ የሚሠራ::

76. እፍ ቢሉት አይነድ፣ እፍ ቢሉት አይጠፋ
እንደ እሳት አይጫር ሲበራ ቀልጣፋ
ደጅ ሲበራ የሚያድር በዝናብ አይጠፋ
ሲነቡት የሚገድል ሰውን የሚያጠፋ፣
ነጮች ያበጁታል ሐበሻ ሳይለፋ::

77. የአጼ ምኒልክ ዘር መዓት ወረደባቸው
የቤታቸው አሽከር እንደ ጤፍ ዘራቸው
ጠንካራ ሰው ጠፍቶ ምች አደረቃቸው
ቀብሩ እንዳይታወቅ ሰው እንዳይቀብራቸው
እያሱ እንኳን እንዳይተርፍ በቅናት ፈጃቸው::

78. አልጋው ደኅና ሳለ አሽከር ሳይሰፍርበት
ልጆቹን ቢተካ እንዴት ባማረበት
ሰውም ስይደነግጥ ቀን ሳይጨልምበት
(ሐበሻ በሞላ ሰውም ሳይመክርበት)
እሱም ይኖር ነበር በለዛ በክብረት::

79. የምኒልክ ዘር አልቆ መነን ትቀራለች
ተፈሪን አግብታ ዱቄት ትወልዳለች
ልጆቿም ያልቃሉ እሷም ጉድ ታያለች
የባሏን መከራ ሳታይ ትሞታለች
ሐበሻ የዚያን ቀን ትነፋፍሳለች::

80. መነን ልትሞት ትንሽ ቀን ሲቀር
ሸዋ በተለየ ይሆናል ሽብር፣
አልጋውን ለመያዝ ለመወዳደር
መቼ ይዘገያል የሰው ደም አይቀር
እጃቸው ይያዛል አያገኙም ኸይር::

81. ተፈሪ መኮንን አሥመራ እጁን ሰዶ
ትግሬን በጠቅላላ አደረገው ባዶ
ዘለዓለም እንዲኖር በሐዘን በመርዶ
እኩሉም ይኖራል ቤቱ ነዶ ነዶ
እኩሉም ይሄዳል ወደ ገርብ ተሰዶ::

82. የትግሬን መከራ የወሎን ችግር
የሚበላው አጥቶ ኸልቁ ሲቸገር
ሐበሻ የዚያን ቀን የለውም ቀራር
ውሸት እንዳይመስልህ በወሬም አይቀር
ያችን ቀን ካለፈ የለውም ችግር::

83. ወሎ በረሃብ አልቆ ሞት የበዛ እንደሆን
የሸዋ መኳንንት ዳርቻው ምን ይሆን?
(በቁም ይጋለጣል ይሆናል እንዳይሆን
ተፈሪ የዚያን ቀን ምን ይበጀው ይሆን?)
የጁን አግኝቶታል እንግዲህ ሰው አይሆን::

84. ተፈሪ መኮንን የተያዘ እንደሆን
እንግዲህ ሐበሻ ምን ይበጀው ይሆን፣
(እህል ያልገዛ ሰው ምን ይበጀው ይሆን?)
አሥመራና ሸዋ ይሆናል እንዳይሆን
ወያኔ ተነሥቶ አሥመራ እሳት ሲሆን::

85. ጋላና ጉራጌ የሸዋ ሙንኪር
ሌት እንቅልፍ የላቸው ቀኑን በነገር፣
ሸዋን ይይዙታል አንድ እንኳን ሳይቀር
ድንጋዩን በድንጋይ አድርገው ንብርብር፣
አጃኢቡን ሳላይ መሬት ስትሆን ብር::

86. ካለፉት ይሻላል ለማልማት ነው እንጅ
ተፈሪ መኮንን ለእስላም አይበጅ
እኩሉን ሲያስለቅስ እኩሉን ሲያበጅ፣
ሃምሳ ዓመት ይነግሣል ዘር የለውም እንጅ
እንቁላሉ ገምቶ ጠፋ በሰው እጅ::

87. ተፈሪ መኮንን ትልቁ ልጃቸው
አልጋውን ለመያዝ ያስባል ልባቸው
የኋላ የኋላ ከቲማም የላቸው
ሸዋ ክፉ ሰው ነው ከሥር ነቀላቸው
ዳግሚያ እንዳይገኙ ከእነልጅ ልጃቸው::

88. አልጋው በወደቀ በሁለት ዓመት
ፊንጭር ፊንጭር ይላል አይሆንም መስሎት
ለዕለት ደስ ይለዋል ያገኘሁ መስሎት
ማለቁን ሳያውቀው በረሃብ በጥማት
ጌታውን ይገድላል ቦታና መሬት
ሀብታም የዚያን ጊዜ ይወድቃል መሬት::

89. ባሪያ ሁር ተብሎ ከሆነ ፈራጅ
ገላጋዩ ማነው? እርስ በርስ ሲፋጅ
የድህነት አዋጅ ሲታወጅ አዋጅ
ተፈሪዋን ጥላ ጅብ አበቀለች
አንበሶቿ ሞተው ባዶዋን ቀረች::

90. ከአሕመድ ነጋሽ አገር አንድ ሰው ተወልዶ
ሸዋ አልጋው ቢናወጥ ሄደ ባሕር ማዶ፣
መሄድም ችግር ነው ቢያዝ አይ ምን ገዶ?
ሐበሻ ጉድ አየ አንበሳ እባብ ወልዶ፣
ትግሬ መርዙን ተፋው ሻንቅላ ጅብ ሰዶ::

91. ቀልድና ዛዛታ በውሸት መማማል
እቤት ሲያሳስቁ ከሴት ጋር መዋል
ዲኑን ለማጥፋት ነው የያዙት ትግል
እሱ ተካ ይላል ባሏ ወጣ ሲል
የሐሳሉን ዕቃ ገብቶ ሊያማስል::

92. ምክሬን ሰምተህ ያዘው የመንደር ውርጋጥ
መጭውን አይተነዋል እንዳትደነግጥ
ሴቶች ያስበቁሃል ስትቆናጠጥ
የአባወራውን ምስት ቀሚሷን ስትገልጥ
እንደ ፍየል ቅልጥም ከንፈሯን ስትመጥ::

93. ዕድሜውን ሁልጊዜ ከእኔ ከተጣላ
ደንዳናው ኢ.ማኑ ይሆናል ነጠላ
ባዶውን እንዳቀር ተጭኖ እየበላ
ቃልቻን ተው በሉት ጠንብቶ እንዳተላ
እንዴት ይሐስደኝ ጠጥቶ እየበላ?

94. ቃልቻን ተው በሉት ደም ሳላስለቅሰው
እባክህ ጌታዬ አታጣላኝ ከሰው
ሳይደርሱት ይደርሳል መቼም የተላሰው
ኢ.ማኑ እንደ እንቁላል ፈርጦ የፈሰሰው
በየደረሰበት ቀልብ እየጠበሰው::

95. ሸዋ መርዙን ገዛ መሪውን ሳይተካ
ወያኔ አስፈራርቶት ንጉሥ እንዳይተካ
መዝረፍ እንዲመቸው ቦታና ፈረንካ
እንዴት ሰው በአገሩ ደም ለውሶ ያቡካ?
ጥይት እህል ሆኖ ሐበሻ ላይ ቦካ::

96. ቦታና መሬቱን ከተወሰደበት
ወዲያው መዓት ይወርዳል እርስ በርስ ጦርነት
በአማራ በእስላም ይገባል ድህነት
በተለይ አሥመራ ትሆናለች ዱቄት
ሸዋ ጠላት ገዛ ጥይት እረከሰበት::

97. ተፈሪን አውርደው ተፈሪ ከገዛ
ለትንሽ ቀን እንጂ እጅግም አይገዛ
ለዕለት ተጠንቀቀው አይምሰልህ ዋዛ
በጉልበት ካልሆነ በፍቅርም አይገዛ
ኋላ ግን ሟች ናቸው ነገሩ ከበዛ::

98. መሳፍንት ከሞተ በሸዋ መዲና
ችግር ይፈጠራል አገርም አይቀና
ሐበሻ የዚያን ቀን አያገኝም ጤና
መለፍለፍ ነው እንጅ አዋጁም አይጠና
በለው ቶሎ አይበርድም ደም ተቃብቷልና::

99. ተዳፍና ስትኖር የአሥመራ እሳት
ማንም እንዳጭራት በውሃ ሲያጠፉት
በግድ አነደዱት የሸዋን ቅርጫት
ኋላ ግን ያራሉ እንደ እሳት እራት
ሸዋ ጦሩን ሰዶ አጣበት ብልሃት::

100. ተፈሪ መኮንን እንዴት ያለ ሰው ነበር?
መረታቱን ሲያውቀው እርቅ ይወድ ነበር
የወደቀው ይውደቅ ብሎ እንዲህ ሊደናገር
ምን ይበጀው ይሆን ከተማ ባላገር?
ዲንህን አጥፍተህ ዘመድክን ሳትሰትር::
101. መሸነፉን ሲያውቀው ጀግና እርቅ ይወዳል
እርቅን እምቢ ካለ አገሩ ይናዳል
ፍቹን ድረስበት እርቁ ይሻልሃል
የተፈሪ ይብቃ መዓት ይወርድብሃል::

102. መወለድ ደግ ነበር ሸዋ ጠፋ ውልድ
አስኮላ ግባ አሉት ኋላ እንዲህ ሊነድ
ልጁን መቅጣት ነበር ብልግናን ሳይለምድ
ሳዱላ አበላሽቶ ትንባሆን ሳይለምድ
ምኑ ይነወራል ሰው ቢገላምጥ፣ ቢያዋርድ
የአማራ የእስላሙን መብላት የለመደ::

103. ሐበሻ ላም ሆና ታስራ ከታለበች
ጡቷን መዥገር ወሮት ጥጃዋን ገደለች
ላምዋም ትሞታለች እየመነመነች
ወተት ቢሉ አይገኝ አንደዜ ሙታለች
ይዘገያል እንጅ ኋላ ትድናለች::

104. የሐበሻ መሬት ሌት ቀን ሲጨልም
ሐረር ወዲያ ማዶ ይፈሳል ብዙ ደም
ቂሙም አይረሳ እስከ ዘለዓለም
መንገድ ይፈልጋሉ ሐበሻን ሊቀሙ
ከስንቱ ጋር ይሆን ሐበሻ እምትገጥም?

105. ቋንቋቸው ተብታባ ዲናቸው እስላም ነው
አገራቸው ቆላ ልብሳቸው ግልድም ነው
ጦራቸው ክፉ ነው አፈር የሚያስቅም
እኒህ ለሐበሻ መርዝ ናቸው ሹ(ስ)ም?
ከኒህ ጋር መጣላት የለውም ጥቅም::

106. በአሥመራ ወያኔ ከመጣ ችግር
መጀመሪያ አሥመራ ትሆናለች ቀብር
አክሱም ትጠፋለች በአንድ ቀን ጀንበር
ግሼን ላሊበላ ትሆናለች ቀብር
ሁሉም ይሸፍታል ሴት እናኳን ሳይቀር::

107. ስንት እጃኢብ ያያል በዱኒያ የቆየ?
እኛ ባንደርስበት የልጅ ልጅጉድ አየ
ጥበብ እንዳይለምድ አሻቅቦ እያየ
የነጮችን ሥራ ብልግናን ገበየ
(አባቷም ዝም አለ ፈርጇን እያየ)::

108. የሳዳቶች ቀለብ ቀንበጥ ሳትረክስ
አላፊው ሳይቅማት ሳትበሰብስ
ትንባሆ ሳይቅማት ተሸጣ ሳትረክስ
ተው አታበላሻት ወንድሜ እየቃምክ አልቅስ
አላህ እንዲያለብስህ ሸማና ቀሚስ::

109. ይሰማኝ እንደሆን ፉቅራን ልምከረው
ለሴት ጫት መቃሙን መትፋቱን ይተው
መብራት አጥፉ እያለ ሰው እንዳያየው
እኔም ዝም አልልም ዲኑን ሲያረክሰው
እንኳን አላህ ጠልቶት ደስ አይልም ለሰው::

110. ብዙ ጉድ አየሁኝ መጅሊስ ተጠርቼ
ቱፍታ ልትመታ ጅስሚን ገልጣ አይቼ
ጸጉሯንና ጡቷን ሲይዟት አይቼ
እራቅ ብዬ ቃምኩኝ እንዳልነካት በእጄ
ሰው ነገረኛ ነው ሐሜቱን ፈርቼ::

111. ጠጅ ጠጣ ይለኛል ሲሩን ሳያውቀው
እኔ ለጠጣሁት ምን ቅናት ያዘው
አላህ ሲይስተው እንጅ ለሰው ብዬ አልተው
ንገሩት ቃልቻን ኋላ እንዳያመው
እንደ መምሬ ጉርሙ ሳላበላሸው::

112. አምስት ወቅት ሶላት ስገድ ብንለው
መርቅኛለሁ አለኝ እዩት ይህን ሰው
ጫቱን ዋጀብ አርጎ ዲኑን ሊያጠፋው
ጫቱን እየበላ ቢሰግድ ምነው?
እኔም ዝም አልልም ዲኑን ሲያረክሰው::

113. ሶላት ካልሰገደ አብሮኝ እንዳይቅም
ሐድራ ያበላሻል የለውም ጥቅም
አይሰግድም ከመባል ሞት አይሻልም
አላህ አይለቀውም እስከ ዘለዓላም
ነገሬ ካልገባው ይጠይቅ ዓሊም::

114. የመተማን ትተን የሐውሳን እናውጋ
ሦስት ቀን ጨልሞ በአራተኛው ነጋ
ለዕለት ታግሎ ነበር ሐውሳ እንዳይወጋ
ስሙ የታወቀ ትልቅ ባለጸጋ
ሳይያዝ ያመልጣል ሐውሳ ግን ተወጋ::

115. ነገሩ እማይገባ የተወላገደ
በአሥመራ በትግሬ ሄዶ እየነደደ
እንዴት ያለ እሳት ከሸዋ ነደደ
ቢያጠፉት እምቢ አለ እየተዛመደ::

116. አንበሳ እግሩን ታሞ ደም ሲያለቃቅስ

ማማው ምስጥ በልቶት ይሆናል ብስብስ
ወደቅ ወደቅ ይላል ወፉን ሊያጨርስ
የዚያን ቀን አሳማ ይሆናል ንጉሥ
ሺምጦ የሚበላ ሰው የሚያስለቅስ::

117. ተፈሪ ክፉ ነው ልቡም አይገኝ
ለሰው ይመስለዋል ይናገራል ቀኝ
ኋላ እንዲህ ሊዋረድ ፍዳውን ሊያገኝ
እሳት ሰደዱበት ዳግሚያ እንዳይገኝ
ዘላለም የማዝበርድ በደም የሚያዋኝ::

118. የተማረ ወድቆ ደንቆሮው ከገዛው
ማን አለብኝ ብሎ አገሩን ወረሰው
ጥሩ አርጎ ባለበት በገዛ እጁ ናደው
ምድር ሊቆረቁር ኋላ እንዲህ ሊቆጨው::

119. አላህ ዝም ብሎ መንግሥት ሊያሳስት
ሰው እንደፍሪዳ ሲታረድበት
ምን ይችል ሐበሻ ጉድ አጃኢበት
በጦሩ ጨፍጭፎ ላይረጋ መሬት
እንኳንም አልደረስን ስትነድ መሬት::

120. አሥመራ ልትጠፋ ገመዱ ሲላላ
በሸዋ ከተማ ይኸለቃል በላ
በሦስት ቀን ይያዛል ጎንደር ላሊበላ
አክሱም የዚያን ጊዜ ትሆናለች ሌላ
ማርያም ትጠፋለች አያዋጣም ብላ::

121. ምን ኑሮ ይገኛል መንግሥት ከከፋ
ሰውን ለመግደል ጦሩን ከአስፋፋ
ውሸት እንዳይመስልህ ይሆናል በይፋ
ጠብቀው ዘመኑን እንዳታንቀላፋ
ወቅታቸው እስኪቀርብ እስኪዘልቅ በይፋ::

122. አይጥ ጠብመንጃ ይዞ ከገባ ከዋሻ
ሳትታይ አትቀርም አሥመራ አላህ ቢሻ
በደም ተጨማልቋል ትሆናለች እርሻ
ብዙ ሰው ይጠፋል ሳይገኝ ወጌሻ
ክፉ ነፋስ ነፍሶ አልብሶት ቆሻሻ::

123. የአሥመራ ወያኔ ከያዘ ጠመንጃ
ደንግጦ ይሞታል የአሥመራ ስልቻ፣
የኋላ የኋላ ከቲማውን እንጃ
ምን አስለፈለፈኝ ላይገኝ ፈረጃ
ነስሩም አይታወቅ ዘላለም ጦር ብቻ::

124. የአሥመራ ጦርነት ታኅሣሥ ሲጀምር

ብዙ ሰው ይጠፋል ነገሩ ሳያምር
አይሰድም መስኳቸው ሸዋ ብዙ ጦር
ወዲያው ሰደዳቸው በሰማይ በምድር
ወያኔው ይሞታል አያገኝም ነስር::

125. ቀልባቸው ነጃሳ ስማቸው እስላም
ንጉሣቸው ሰወው ይበላል ጅም ላም
በስሙ የሚመራ ዓለም ለዓለም
ለዲን ተቆርቋሪ ለሁሉ የሚጠቅም
በኋላ ያልቃሉ ቀኑ ሲጨልም::

126. ባሕር ወዲያ ማዶ አራት ሰዎች አሉ
ከእነዚህ ሁለቱ በቀንድ ይበልጣሉ
የጌታችን መቃም አየነው ባይሉ
ለአዳም ፍጥረቶች በላዕ ይሆናሉ
በአመጡት በላዕ እነሱ ያልቃሉ::

127. ሐበሻ ሁለት ነጭ ሳይገቡም አይቀር
አንደኛው በፍቅር አንደኛው በጦር
አስበው ነበረ ሊያረጓት አገር
አምስት ዓመት ገዟት ሲል ደንገር ደንገር
እኩሉን በሥራ እኩሉን በጦር::

128. ዘመን ተበላሽቶ ወደቅ ወደቅ ሲል
ነጭ ከባሕር መጥቶ ይስላሉ ሲል
ተፈሪ የዚያን ቀን ይሆናል ትል
ሜዳ ላይ ይወድቃል ሳያገኝ ጅልል::

129. አላህን ሰደብኩት ማን አለው ጠበቃ
ምን ሥፍራ ኖሮት ነው ለራሱ የሚበቃ
በዱኒያ እንደሆነ ይበልጣል የእኔ ዕቃ
ቃልቻ ይመስክር አላህ ካለው ዕቃ::

(ከገጽ 130 — 136) ያሉት አልተገኙም ወይም አልተጻፉም ???

137. አውራ በሬ ታርዶ አንበሳ ሲያለቅስ
ሐበሻ የዚያን ቀን ትሆናለች ኩስ
ሽታዋ የሚያስከፋ የምታስነጥስ
የዚያን ዕለት ይወድቃል እስላምና ቄስ
የዚያን ቀን ያስፈራል አገር እንዳይፈርስ::

138. እኛ አፈር በገባን በአንድ መቶ ዓመት
ተፈሪ ዓይኑን ታሞ ይገባል መሬት
ማር የላሰ ሁሉ ይቀምሳል እሬት
የበላውም አይቀር ሽቅብ ሲያስተፉት
ካለው ይገድሉታል ለገዘብ ስስት::

139. ሸዋ እባቡን ሳይዝ ምስጢሩን በዝብዞ
ድርቡሽ አገር ገባ የሰውን ላብ ይዞ
እባብ ልቡ አይገኝ መጣ መርዙን ይዞ
ዓለሙ ላይ ተፋው ያገሩን ጅብ ሰዶ
አብሮ የሚበላ አንጀትን በዝብዞ::

140. ሷሊህና ቃሲም አብደላህና ዙበኗር
በወልቃይት ብቅ አሉ ትግሬ ሲበረበር
ኩታበር ገራዶ ትሆናለች ጠጠር
ጎጃም ትጠፋለች ሳትውል ሳታድር
ብዙ ሰው ይጠፋል ያውም ከባላገር::

141. አሥመራ ተወግቶ ወልቃይት መርዙን ተፋ
ሽሬና መቀሌ ይሆናል የከፋ
እንቅልፍ እንዳይወስድህ እርብ ሳይጠፋ
ይመስላል ላየው ሰው ቂያማ የተደፋ
እርብ ስንቱን ጣለው ጠብቆ ወረፋ::

142. ጋይንት ንፋስ መውጫ ድራና ፎገራ
እርብ ላይ ሞልቶ ሲዘፍን ሲያጎራ
ነጋዴው ይጮሃል መቀሌና አሥመራ
ምን ይበጀው ይሆን ጅልጋና ፎገራ?
ሸዋ ደፈረሰ እህሊን ሳይዘራ::

143. መግዛቱን ይገዛል የዮሐንስ ዘር
ወዲያው ለጥቂት ቀን ይላል ፈንጨርጨር
ተፈሪን ጥላ አርጎ ሲያሳድድ ሲቀብር
ቢያዝ ደግ ነበር አገሩን ሳይቀብር
በቀር ሸዋ አይረጋም አትጠራጠር::

144. ሐበሻ ተፈሪን ይዘው ከቀበሩ
አሥመራ በሞላ ይታጠራል በሩ
መቼም ላስተዋለው ብዙ ነው ነገሩ
እኔ እገሌ አልልም ብዙ ነው ምሥጢሩ
በጫካ አካባቢ መች ቀረ ነገሩ::

145. ሐበሻ ስትደኽይ ስትቀጥን እንደ ድር
አዲስ መንግሥት ወጥቶ ይታደላል ምድር
ኸልቁ የዚያን ጊዜ ይለዋል ደንገርገር
ገንዘቡን ተወርሶ አታክልቱም ሳይቀር
እንኳን የተከለው የበረኸው ሳይቀር::

146. ይኸ ቻይና እሚሉት ዘራቸው ካልጠፋ
ችግር ይፈጠራል ይሆናል የከፋ
ማጥፋት ይሻል ነበር በአገር ሳይስፋፋ
ወልደን ሳንጥለው ልጃችን ሳይጠፋ
ጠብቀው ዘመኑን እስኪታይ በይፋ::

147. ሐበሻ ከገባ የቻይና ቁራሽ
ዲንን ያስፈራዋል እንዳይሆን ብላሽ
የዘመኑ ወጣት በሆኑት ቆስቋሽ
ስንቱን አደረጉት ደህይቶ እንዲሸሽ
እንዳይጣቀሙ ሀብታምና አራሽ::

148. ምን መላ ይገኛል ጦር ቢያከማቹት
አልገዛም ካለ ከወንድም ከሴት
ሸዋ ካልመከረ ይሆናል ወንፊት
እባብ መርዙን ከተፋ ይመጣል ፍጅት
ይህን እየሰማህ እንዳትገባ እሳት::

149. በድርቡሽ ሲገርመኝ የመተማ እልቂት
የማይጨው ሲገርመን የአድዋ ጦርነት
መቀሌን አየሁት አረሁ በልቶት
ሸዋ በገዛ እጁ በጫረው እሳት
ስንቱ ሰው ይነዳል ውቅሮ አዲግራት::

150. እንኳን የአንበሳ ልጅ እባብ ሲዞረው
ጀግና የሚወጣበት አገሩ የት ነው
ሥፍራውን ለይቼ እኔ ሳስታውቀው
ሽሬ ልጅ አንበራ ማይጨው ወያኔው
ምኒልክ ይመስክር ሲዋጋ ያየው::

151. የወልይ ልጅ ወልይ፣ የጀግና ጀግና ነው
እኛ እንኳን ባንቀምሰው በሌላው አየነው
በልተው እየጠጡ ጅስማቸው ቀጭን ነው
ወትሮም ደኅና ኅበዝ አካለ ቀጭን ነው
ተፈሪ የማይወፍር ሐሳብ በዝቶበት ነው::

152. ሸዋ አሥመራን ፈጅተህ አቃጥለህ በእሳት
ማምለጫም አታገኝ ሁሴን ፈረድኩት
ግን አሥመራ ያልቃል በራብ በጥማት::

153. ሐበሻ በሞላ በጦር ከተመራ
ወቅትታቸው ያበቃል ፉቅራና ደብተራ
ለአገር ባይመቹ የሚሠሩት ሥራ
ምድር እያሳዩ ሲያስጥስ ደንቃራ
ጉዳቸው አያልቅም ቢወራ ቢወራ::

154. አሥመራ በጥጋብ ሲዘል ሲደነፋ
የልቡን ተናግሮ ገንዘቡን ሳያጠፋ
እስላም ከክርስቲያን ከሁሉም አይጠፋ
ሁሉም ሊከፋበት በረሃብ ሊያንቀላፋ
ወቅቱ ዘንበል ሲል ያለቅሳል በይፋ::

155. በርበሬ ቢጋገር እንጀራም አይሆን
አዟሪው ማን ይሆን አፍሳሹ ሊጡን?

አቡኪው ማን ይሆናል የሚሰድ እጁን
ሸዋ ግን አይፈራም ያውቀዋል ግዱን
በልቶ ሰው ያስባል እስኪገን አማን፡፡

156. የከተማ ወንፊት በርበሬ እየነፋ
ንፋስ የመጣ እንደሁ ነፊው ዓይኑ ጠፋ
ዓይኑን እስከሚያሸው ነፊ አጥቶ ተደፋ
ንፋስ እያየ ነው በርበሬ የሚነፋ
ፍሬው ካልወደቀ ገለባ አይነፋ፡፡

157. የአሥመራን ልቅሶ ሸዋ ካልሰማው
እንደ ጥቅምት ማር ይልሰዋል ሰው
የጠገበው ኀበዝ ቁንጣን የነፋው
ይጨፈጭፈዋል ዳግሚያ እንዳይለምደው
ቤቱን እስከሚያገኝ በግድ የቀማው፡፡

158. ከቴዎድሮስ አንስቶ ተፈሪ ድረስ
የመኑ ያበቃል ዘውድና ንጉሥ
ንጉሥ አለ ብለህ አትወሳወስ
በምርጫ ካልሆነ የለም የሚነግሥ
ግን ሰውን አየሁት ብዙ ቀን ሲያለቅስ፡፡

159. እያሱ ተረግሞ ሰክሮ ሲያንቀላፋ
ተፈሪ ይነግሣል ሳይደክም ሳይለፋ
ቀጥሎ ያውጃል እንዲያውቁት በይፋ
ፈረንጅን ድል አርጎ ተይዞ ሳይጠፋ
ዘለዓለም የእሱ ናት እስኪሆን አንጋፋ፡፡

160. ሐበሻ ክፉ ነው ቀርጦ ከተነሣ
ፈረንጅን አረጉት ባንዴየ እንዲነሣ
ጦርነት አስቦ ዳግሚያ እንዳይነሣ
አገር መች ይቻላል ቀርቶ ከተነሣ
ሲያዩት ሞኝ ይመስላል ሲነሣ እንደ አንበሳ፡፡

161. እንደ እንቁላል ገምቶ ሲፈርጥ እንደ አምቧይ
ምን ይበጀው ይሆን ባለዛር ጠንቋይ?
ሳትያዝ አትቀርም ዕዳህን ሳታይ
ምን ጠንቋይ ይባላል መጪውን የማያይ
እኛ ባንደርስበት ምንቅሩ ሊታይ፡፡

162. አሥመራና ትግሬ ስትል ሰገደይ
እባብ ከተፍ ይላል ማምጫው ሳይታይ
ሸዋ የዚያን ጊዜ ይላል ዋይ! ዋይ!
ጀርባውን ምች መታው ወደ ትግሬ ሲያይ፡፡

163. ሲተክሏቸው ጥሩ ሲበቅሉ ጠማማ

ታመጣው ይሆናል ወይንስ ከማማ
አላህ ያሳያችሁ የወሎ ኡለማ
ደረጃው ምንድን ነው? ቃልቻው ሰው ታማ
ግን ኋላ ላያቸው ይሆናሉ አሳማ::

164. እንግዲህ የእኔ ጠጅ ነገር ካመጣሽ
ቃልቻ ይጠጣሽ ይታጠብብሽ
ሌላ ሳትነኪ ሐሲድ እያየሽ
ሰው እስኪስቅበት እስኪሆን ብላሽ
በስተቀር ወላሂ ዳግሚያ ላልቀምስሽ::

165. እንግዲህ ቃልቻ አትጫወትብኝ
አንተ እቤቴ ቀርተህ ምንድን ጎደለብኝ?
ትዕቢትህ በስተቀር ሌላ ምን ቀረብኝ::

166. በላ አላህ ይሁንህ የመንደር ቃልቻ
ይኸው አድርገነሃል የቋንቋ ስልቻ
ከቤት እንዳትወጣ ሁን እንደ ጉልቻ
ሴት ወንዱ ያዋርድህ አታግኝ ፈረጃ
በልተህም አትጥገብ ሁን እንደ ስልቻ::

167. የሐበሻ አውሊያ ያሳያችሁ አላህ
እኔ እገሌ አላልሁም በድፍን ሺሊላህ
መቀመጫ አጣሁኝ በቃልቻ ታማሁ
ከፍርሐል በዟሂር አሉኝ ጠጅ ጠጣህ
ከስንቱ ልጣላ አረ የአላህ ያለህ::

168. አላህ ገላገለኝ ዘለዓለም ወይኔ ስል
ቢነግሩት አይሰማ ቢጥዱት አይበስል
እሳት ሰደድኩበት በጣም እንዲበስል
ሲያሰፋ ይኖራል አበያ ይመስል
ግን በእኔ ካልመጣ አልገድልም ለሰው ስል::

169. አሽሙር ነው ነገሬ እንዳትሳሳት
አፈር በገባን በአርባ አምስት ዓመት
በሐበሻ መሬት ይመጣል ፍጅት
አውሊያ የተባልክ በደጎና ሰንብት
ዚያራው ያስፈራል መኮች ባወሩት::

170. ወልይ የለም ካሉ የኸልቁን መብራት
መኮች ባወሩት መንገድ እንዳትሳሳት
ሽሊላ በላቸው ከወንድም ሴት
በዟሂር ከሞቱት በዱኒያም ካሉት::

171. አለህም እንዳልል ሥፍራህን ማን ያውቃል?
የለህም እንዳልል ሥፍራህን ማን ያውቃል?

እንዴት የአንተን ሥፍራ ሸይጧን ይደፍረዋል?
ወትሮ ጭቡ ሱሪ ሰው ያስወነጅልሃል
ያልሆነውን ሆነ እያለ ያወራል::

172. ከአሜሪካ ወዲያ አለ ጥሩ ባሕር
ሃያ አምስት ያስኬዳል በግምት በእግር
ከዚያ አንድ ጎራ አለ ተተክሎ እንደ ጦር
ነጮች ከዚያች ሥፍራ ሳይደርሱም አይቀር
ላዩ ግን ሜዳ ነው የአንድ ጋሻ አገር::

173. ከአሜሪካ ወዲያ አለ ጥሩ አገር
ተራራውን ወጥቶ ከተገኘ ቀድ(ጽ)ር
ላዩ ግን ሜዳ ነው የሚያጭበረብር
ሥፍራው ከንዝ አያጣም ለሆነ ዘኪር
እዚህም አይደርሱ እንኳን ከቀመር::

174. ነጮች ሄዱ.ል ካሉ ነጭን ከጨረቃ
መወሊድ የለም ካሉ ዚያራ ሰደቃ
ነቢን ከጠሏቸው የኸልቁን ጠበቃ
እንኳን ማውራት ቀርቶ መስማትም አይበቃ
ልባቸው እርኩስ ነው ሥራቸ ጨምላቃ::

175. አምስተኛው መዝሕብ ተሺጦ ሲለማ
ኋላ ጉድ ታያለህ የወሎ ኡለማ
የማታውቀው ነገር ቀርቧል ልትሰማ
ሰምተህ እንዳትከፍር ጆሮህ እየሰማ
አሚት እንዳይረግምህ አህያ ስትሰማ::

176. ( **የተዘለለ ወይም ያልተጻፈ**)

177. ምስክር የለኝ ተናግሬ አልሸሽ
አዋጁን ተከተል ሳትከፍር ብላሽ
በሁለት መንግሥት እንዳትቆሸሽ
ያሲን መስክሮታል ቁርዓንም አይዋሽ
ሌላ ካልፈሠሩት ሰው እንዲበላሽ::

178. በአምስትና በአራት በሦስት ሰጠር
ሲከትበው አየሁት ሼህ መሐመድ ኑር
ቆንጥሮ ያወራል መንደር ለመንደር
ጠቅላላ ሳይዘው ቀርቶ ሳይከርር
ሰውን እያየሁ ነው ጠልፎ ሲናገር::

179. ፈረስ ደጎና ሰንብት አላህ ይሁንህ
ነጭ ሐበሻ ገብቶ ጉድ አሸከመህ
የናታውቀው ነገር ጭኖ አስጎተተህ

ጉድክን ወደ ኋላ እንዳታይ ሆነህ
በአንዱ ስታለቅስ ሦስት ሰው ጫኑህ::

180. አረብ አገራችን ሳይለምድም አይቀር
ወልደው ይከብዳሉ ያደርጋሉ አገር
ግን ልጁ ሽይጣን ነው አንድ የለውም ኸይር
ሶላትም አይሰግድ እንደ ዱር ሲቀር
መልከ ቆንጆ አይመርጡም ብትሆን ባሪያ ኩፍር::

181. ሀብታም ወራሽ መንግሥት ተሹሞ ሲመጣ
ሙክት የዚያን ጊዜ ይሆናሉ ቋንጣ
ሁሉም ይጎዳዋል ፀሐይ እስኪወጣ
ታስሮ ከመገደል ምናልባት ቢወጣ
የአላህ በል የዚያን ቀን እንዲህ ያል ሲመጣ::

182. ዘመን ተለውጦ ጥቅምት ሲደርስ
በአሥመራ ከተማ ይነፍሳል ነፋስ
የዚያን ቀን ሐበሻ ይላል ፈረስረስ
ሃምሳ ቀን ይቆያል ሴት ወንዱ ሲያለቅስ
ወንፊት ጉድ እስኪወልድ እስኪሆን አራስ::

183. መንግሥታቶች አሥራ አምስት ሲቀሩ
ከድንጋጤ በቀር ይርቃል ኸይሩ
በረካም አይገኝ እስኪ ቁርዓን ቅሩ
መድፈርም አይበቃ ደብዳቤ መቅበሩ
ለሰው ግን ጥሩ ነው በአማን ማደሩ::

184. በመካ አንድ ንጉሥ በገርብ ሦስት ሲቀር
ድርቡሽ የዚያን ጊዜ ያስባሉ ሽር
የዚያን ቀን ያየ ሰው ሲጫጫር
በሰበቡ አሥመራ ትሆናለች አር::

185. እኛ አፈር በገባን በስድሳ አምስት
ንጉሥ የተባለ የለውም ሐያት
እጁ እየተያዘ ይገባል እሳት
ዘሩ እየታደነ እንደ አውሬ እንደ እሳት
ከእኛም ሳይመጣ አይቀር ኋላ ወደፊት::

186. አጼ ኢያሱ ነግሦ በሸዋ መሬት
ጥቅልል አርጎ ይዞ የአያቱን ግዛት
በኋላ እንደገና አላህ ሽቶበት
ዘኒ ሆነ ብለው በቀን በሌሊት
አይቶ እማይለቅ ሆኖ የምታምር ሴት
እንኳን ሌላይቱን እህቱን ጣላት

በኋ በሌለበት እሱ አስረገዛት
ከአልጋው ያወርዱታል በሥራው ክፋት::

187. ለጥቃ ተሾመች ዘውዲቱ የሚኋት
ሦስት ዓመት ገዛች ይች ቆንጆ ሴት
የራስ መኮንን ልጅ ተፈሪ የሚሉት
መቃ ሠራ በሷ ገድሎ ቀበራት
እቤት ውስጥ ቀብሮ መደብ ሠራባት
በመቃ ይሎታል መች ሲቀርለት::

188. ታ(ተ)ጥቆ ተሾመ ተፈሪ አባ መላ
ሃምሳ ዓመት ይገዛል ሐበሻን በሞላ
የሚገዛበት ነው በብልሃት በመላ
ባይሆን ቀኑ ሲደርስ ሃምሳ ዓመት ሲሞላ
የገዛ አሽከሮቹ ያዝ አርገው በመላ
ከአልጋው ያወርዱታል በችግር ሊቆላ፣
ከዚያ ያበሉታል ቸኮሌ ባቄላ
ችግረን ቅመሰው ጮማህን ሳትበላ::

189. ሕዝብን ስትቀጠቅጥ ለድሃ አታዝን
ክብር ስታሳዳግ አርገርህ የልቡን
በመሥሪያ ቤቱ ዘመዶችህን
እስኪ ይድረሱልህ እንዲህ ስትሆን::

190. ከአልጋው አምዘግዝገው ምድር ይጥሉታል
ወዲያው የፊጥኝ እጆቹን ያስሩታል
በፊት መቃ መሥራት እንዲህ ያንገላታል
ከሞላው አሚሚት በእሱ ይበረታል
ሳያስበው ድንገት ከአልጋው ያወርዱታል::

191. ቸኮሌ እያበሉ እልፍኙ ያስሩታል
ሕዝቡን እንደቀጣ ችግር ያበሉታል
መስከረም አንድ ቀን ደንገት ይይዙታል
አሥራ አምስት ቀን ለዓመት ሲቀረው ይሞታል::

192. አንተ በእልፍኝህ ውስጥ በልተህ ጮማህን
ድሃው ቆሙን ውሎ ቀምሶ ጥሬውን
ትንሽ እዝነት የለህ ቅመሳት አሁን::

193. የገዛ አሽከሮቹ ያሳደጋቸው
በዙፋን ባልጋው ላይ ያሞናደላቸው
ከአልጋው ያወርዱታል አላህ ሠልጧቸው
እሑድ ቀን ሰንበቱ እንሂድ ብለው
ዘውዱን ከራሱ ላይ ሉሉን ቀምተው

አመድ ያቅሙታል ትዝ ሳይለው::

194. የዳግሚያ መኮንን የአልጋ ወራሽ አባት
የመነን አስፋው ባል፣ አጼ ኃይለ ሥላሴ ባለ ብዙ ብልሃት
ደርጎች ያወርዱታል ከእልፍኝ ከኩራት
በዘውዲቱ ጡር ውሎ መቃ በሠራበት
ጥቃቱን ይቀምሳል ኩስ እሬት ያለበት
በእሱ ጊዜ ያሉት ሹሞችም ባላባት፣
ከእዛ ያድኑታል ሁሉም በያሉበት
ዱአ አድራጊ ድሁ መቼም ምን የለበት፣
አደብ ካጣች በቀር ጌታችን ሽቶበት::

195. አጼ መባል ቀርቶ አሮጌው ይሉታል
እሬት ኮሶ ቀምሶ አመድ ያለብሱታል
ከአልጋው አውርደውት አልቅሶ ይሞታል
እራሱ ጡር ውሎ መቃ ፌቱ ታለ::

196. አንድ ሺህ ሦስት መቶ ዘጠና ዓመት
አራት መቶ ሳይሆን እዚህ መሃል ናት
ተፈሪ አባል መላ የሚወድምበት::

197. ኃይሌ መቃ ሠርቶ በዘውዲቱ ሬሳ
በሺች መደቡ ላይ ቢሞትባት እሳ
ጌታችን መቼ ነው ጀዛን የሚረሳ?

198. ከአዳም አንስቶ እነቢ ድረስ
ስድስት ሺህ ዓመት ስንት መቶ ምጉሥ
ከነቢ አንስቶ ቂያማ ድረስ
ሁለት ሺህ ዓመት ጌታ ቢለግስ::

199. አንድ ሺህ ሦስት መቶ ዘጠና ዓመት
ሒጅራው ሲሆነው ኸይረል በርየት
አለች ብርቱ ቀን አለች አቀበት::

200. እዝናት የሚጠፋባት ከወንድም ከሴት
ወዳጅም ዘመድም አባትም እናት፣
የወለዱትም ልጅ ውንድምም እኅት፣
እየጠና መሄድ ከአንዱ ዓመት አንዱ ዓመት
እስክትሾልክ ድረስ እርብ የሚኗት
እንዴት ያለች የመን እንዴት ያለች ወቅት?
የጠናች ወራት እህል በቆርቆሮ የመቀናበት
ቡና በችርቻራ የሚሆንበት
በሬ መቶ ሃያ የሚያወጣበት
በሬ አንደ ማሽላ የሚፈጅበት
ጭቃና ምስለኔ የሚሻርበት

ገበያ በሙሉ የሚጠፋበት::

201. እንኳን ሌላው ነገር ወስው ሐታ አድሩስ
ይጠፋል አወል ቡን ሲቀዳ እሚጤስ::

202. አሁን ያልኩህ ዘመን ናት የነዚያ ወራት
ወታደር መንግሥቱ የሚሾምበት
አገር ቤት ሹመቱ የሚገባበት
ወንድ ሴት፣ ልጅ አዋቂ ሁር ባርያ፣ እኩል የሚባልበት::

203. በሰማይ ቀበሌ መላኢሞች ሲያወጉ
በአጼ መባል ቀርቶ ይባላል በደርጉ
ያን ጊዜ በዱአ እንዳትዘነጉ
መሬትና ሹመት እንዳትፈልጉ::

204. ያን ጊዜ ይበጃል ክልል የሚሉት
እንዳይገናኙ ከእነኛ ሐዋይት
ከያዘ በስተቀር ትንሽ ወረቀት
ይህንን ነገረኝ በይሩስ የሚሉት
የዒፍሩት ወንድም ነው በአባትም በእናት
ያዝ ጊዜ ይነዳል ውሃም እንደ እሳት
በቅሎም ትወልዳለች መሐንም ከሴት
ሽምበቆም ያፈራል ልጠው ቢያቆሙት::

205. ይህንን ተናግሯል በቁርዓን አያት
ወኢዘል ቢኋሩ ብሎ ሲጅረት
ያን ጊዜ ይበዛል ጦርና ዱለት
ደላንታ ይዋጋል ቦረና መሬት
አላሽም ይዋጋል ኤርትራ እሚሉት
በሸዋ በደሴ የሚያልቀው ፍጥረት
ያን ጊዜ ነበር አላህ የሻለት
ሌት ቀኑን መወትወት ነው በአሕመድ ሶላዋት::

206. ዱአ በቀኝ እጁ አድርጎ መያዝ
ያን ቀን ያድነዋል ከብዙ መዘዝ
ወንድሜ ልንገርህ እንዳትፋዘዝ::

207. ይመጣሉ እነዚያ፣ እነ አይራራ እነጨካኝ፣ ደርጎች የሚሏቸው
ዱአ አድራጊ በቀር የለም የሚችላቸው
እነዚያ ኃይለኞች እነዚያ ጨካኞች
እነዚያ አሽብሮች እነዚያ አንበሶች
በክፉ ያዩትን እነዚያ እርጉሞች
በደግ ለታያቸው እነዚያ ደጎች::

208. ደርጎች አይቀሩም ይመጣሉ፣
ዝመቱ፣ መንገድ ሥሩ፣ መሬትን ክፈሉ እኩል የሚሉ
ሰማዩን በባላ ገድፉት ባይሉ::

209. ደርጎች ኤርትራ ሕዝቦች ጋር ሦስት ጊዜ ዘምቶ
የሰላም ንጉሥ ይመጣል ጥቂት ቀን ሰንብቶ
ስድስት ዓመት ይገዛል ዲኑን እስላም ነግሦ
ደስታ ይሆናል ለሱስማ አብሶ::

210. በፊት የቀሰለ ያን ጊዜ ያሽራል
ድሉ ለኡስማ ያን ጊዜ ይዞራል
የደርጎች ዘመቻ ኤርትራ በኋላ
በስተጀንበር መግቢያ አለ በመቅደላ::

211. ይህ ዘመቻ ነው አለቃው ዘመቻ
የሄደው አይመጣም የቀረውን እንጃ
መቅደላ ያልኩህ የርብን ጉባዔ ነው::

212. አሥራ ሁለት ኮርማ የሚገጥምበት
የጎበዞች ሥፍራ እርብ የሚሏት
የርብን ጦርነት ልንገርህ ጥቂት
ሰው ይታደላል ስንዴና መሬት
ደግሞ ሁለተኛ ብርና ጥይት፣
ሰው ያበዛል ሐሰድና ውሸት
እርስ በርሱ መዟለም ነው ድርቅና ኩራት
ወራቷም ሚያዚያ ናት ቀኗም እሮብ ናት
ሦስት ሰዓት አንስቶ ሰኞ ድረስ ናት
አዋጁን ልንገርህ እንድትጠብቃት
ዱአ እያደረግክ በቀን በሌሊት::

213. መሬት የምትከጅል ደግሞም ልብስ ጉርስ
ገበያ እንገናኝ መቅደላ ድረስ
የጡርንባው ብዛት ሦስት መቶ ይሆናል
መህሉቃቱ ሁሉ አንደዜ ይሰፍራል::

214. እንኳን ያ(የ)ለው ሰው ጥቂት ልጅነት
ሽማግሌ ባልቴት በምርኩዝ በከብት::

215. ጡሩንባውን ነፍቶ አዋጅ ያደርግና
ወንዱንና ሴቱን ክተት ይልና
በመድፍ በመትረየስ ያንደቀድቅና
ይቆላዋል ከዚያ መኻል ያደርግና::

216. አዋጅ ሊደረግ ሲሉ ክተት
የራሕመት ደመና ያጠለለት
ማቄን ጨርቄን ሳይል አውድማ ክትት
ባቄላ ፍሬ አለች ዲቃን የሚሏት
ስትቀቀል ውላ ፍላት አይነካት
ከርብ መከራ ጌታ የሚያወጣት፣
አንድ ሺህ ሦስት መቶ ከዘጠና ውስጥ
አራት መቶ ሳይሆን እዚያ ውስጥ ናት
የፍጥረቱ አውድማ እርብ የሚሏት::

217. የርብን መከራ ስንቱን ልንገርህ
ቂያማ ቀን ይመስላልገና ሲቀርብህ
ኸልቁ ይሸበራል እንደ ቂያማ ዕለት
ቀኗንም ወራቷንም ከዋሸንላችሁ
እንዳትሄዱ አደራ የእኛ የሆናችሁ
የራሕመት ደመና ሽፍን ያድርጋችሁ::

218. ነቢ ተናግረዋል ኸይረል በርያት
ክፉ ነፋስ አለች ሐበሻ መሬት
ኸልቁን የምትጨርስ ቀንና ሌሊት
ማእናውን ልንገርህ ንፋስ ያልንበት
ሽብርና ጭንቀት የበዛባት ናት
እጦሩ መካከል አለ አሉ ድንገት::

219. ከርብ ጦርነት ወዲያ ያለቸው ሰዓት
ክብረትና አፊ(ሠ)ያ ናት ደስታ ውበት
ምናልባት ብትተርፍ ከሰዎች ጥቂት::

220. ጥሩም በሽታውም መከራው ብዛት
ይበቃል ነበረ የአንድ ማሳ እሸት
አላህ ላደረሰው በዚያች ዘመናት
አባክህ አድርሰን እረቢል (ግ)አዘት::

221. አዱኛ ደኅና ሁኚ ጋሰብኩሽ
ምስክሬ አንቺ ነሽ አዋጅ እንዳትረሽ::

## ዋቢ መጻሕፍት


1. ሐሊማ መሐመድ፣ 1976 ዓ.ም፣ ለባሌው ሼህ ሁሴን የተገጠሙ ግጥሞች:: ለባችለር ዲግሪ ማሚያ የቀረበ ጥናት፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ክፍል፣ አአዩ::
2. ፈንታ ሀ. 1985፣ የደብረ ማርቆስ ሙስሊሞች ቂሳ:: ለባችለር ዲግሪ ማሚያ የቀረበ ጥናት፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ክፍል፣ አአዩ::
3. ኪሩቤል ሸንቁጤ፣ 1984፣ የቃጥባሬው ሼህ ሁሴን የሕይወት ታሪክና የበዓላቸው አከባበር:: ለባችለር ዲግሪ ማሚያ የቀረበ ጥናት፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ክፍል፣ አአዩ::
4. ሙሐመድ ኢ. 1988፣ ሼህ አደም ደርቃና ግጥሞቻቸው:: ለባችለር ዲግሪ ማሚያ የቀረበ ጥናት፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ክፍል፣ አአዩ::
5. ሙሐመድ ጅ. 1984፣ ሼህ ጫሊና የመውሊድ ግጥሞቻቸው:: ለባችለር ዲግሪ ማሚያ

የቀረበ ጥናት፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ክፍል፣ አአዩ::
6. ሙሐመድ ይ. 1986፣ በወረታ አካባቢ በዱአ ላይ የሚባሉ እንጉርጉሮዎች:: ለባችለር ዲግሪ ማሚያ የቀረበ ጥናት፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ክፍል፣ አአዩ::
7. ረታ ዓለማየሁ፣ 1976፣ የወሎ ቃልቻ ግጥሞች:: ለባችለር ዲግሪ ማሚያ የቀረበ ጥናት፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ክፍል፣ አአዩ::
8. ጥበቡ ሰ. 1976፣ የሐጂ ሀሚድ መንዙማዎች:: ለባችለር ዲግሪ ማሚያ የቀረበ ጥናት፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ክፍል፣ አአዩ::
9. ጽጌ ንጋቱ አስቸናቂ፣ 1982፣ የሰይድ ቡሽራ አፈታሪክና የመውሊድ በዓል አከባበር በገታ::ለባችለር ዲግሪ ማሚያ የቀረበ ጥናት፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ክፍል፣ አአዩ::
10. ዑመር ዳውድ፣ 1982፣ በአዲስ አበባ ሙስሎሞች በመጅሊስ ላይ የሚኳቸው እንጉርጉሮዎች:: ለባችለር ዲግሪ ማሚያ የቀረበ ጥናት፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ክፍል፣ አአዩ::
11. ዮሴፍ ሰ. 1981፣ በፋርሲ ወረዳ የወዳጃ ግጥሞች:: ለባችለር ዲግሪ ማሚያ የቀረበ ጥናት፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ክፍል፣ አአዩ::
12. አበበ ኃይሉ፣ 1981፣ የወዳጃ ትውስታ በሐረርጌ:: ለባችለር ዲግሪ ማሚያ የቀረበ ጥናት፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ክፍል፣ አአዩ::
13. ቦጋለ ተፈሪ፣ 1985 ዓ.ም፣ የሼህ ሁሴን ጅብሪል ትንቢታዊ ግጥሞች:: አዲስ አበባ፣
14. _____. 1980 ዓ.ም፣ ሼህ ሁሴን ጅብሪልና ግጥሞቻቸው:: ያልታተመ፣ ለባችለር ዲግሪ ማሚያ የቀረበ ጥናት:: የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ክፍል፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ::
13. Berhanu Gebeyehu, 1998. Islamic Oral Poetry in Wollo: A Preliminary Descriptive Analysis. M.A Thesis. Institute of Language Studies. Addis Ababa University.
14. Ishihara, M. 1996. Textual Analysis of A Poetic Verse in Muslim Oromo Society in Jimma Area, South Western Ethiopia. In: Essays in Northeast African Studies. Senri Ethnological Studies. No. 43.
15. Assefa Mamo. 1987. Some Prominent Features of the Manzuma Genre in Wallo. M.A Thesis. Institute of Language Studies, Addis Ababa University.
16. Alula Pankhurst, 1994. Indignizing Islam in Wallo: *Ajäm*, Amharic Verse Written in Arabic Script. In: Proceedings of the 11$^{th}$ ICES. Vol. I, pp.
17. Hussien Ahmad. 2000. *Islam in 19$^{th}$ Century Wallo Ethiopia*. E.J.Brill.
18. _____, 1988. “Traditional Muslim Education in Wollo”. In: *Proceedings of the 9$^{th}$ ICES*. Moscow, vol. 3, pp.
19. Ficquet, Eloi. 2000. •••• •• ••• •••• ••• •••• Oracles du shaykh Husen Jibril (version de Ali Yemer). Paris.